MCPS MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
www.montgomeryschoolsmd.org MARYLAND

Malcolm Baldrige National Quality Award
2010 Award Recipient

ውድ ወላጆች፣

የMontgomery County Public Schools የበላይ ተቆጣጣሪ ከሆንኩበት ወቅት ጀምሮ፣ ስለ ማህበራዊ ስሜታዊ ትምህርት አስፈላጊነት በሰፊው ተናግሬአለሁ—በመሰረቱ፣ ህይወታቸውን በጤናማ፣ አወንታዊ መንገድ ለመምራት የሚያስፈልጓቸውን ሙያዎች ለተማሪዎቻችን መስጠት። ስለዚህም ነው ዛሬ ለእናንተ የምፅፈው።

በዚህ ሳምንት፣ የዊንተሩ አየር ት/ቤቶችን ለማዘግየት ወይም ለመሰረዝ ለመወሰን በተለመዱት ሂደቶቻችን እንድንጓዝ አስገድዶናል። ቀላል ውሳኔ አይደለም እናም ሰራተኞቻችን በሁሉም ሰአቶች በመስራት የመንገድ ሁኔታንና የአየር ትንበያዎችን መከታተላቸውን አካትቷል። ሁኔታውን በመገምገም ሂደት ላይ እያለን፣ ተማሪዎች በትዊተር አማካይነት ሊገናኙኝ ጀመሩ። ከነዚህ "ትዊቶች" ከፊሎቹ ጮሌ፣ አስቂኝ፣ እና ትሁት ነበሩ፣ መተኛት እንዲችሉ ወይም የቤት ስራቸውን ለመስራት ተጨማሪ ጊዜ እንዲኖራቸው ት/ቤቶች እንድዘጋ የሚለምኑ ነበሩ። በርካታዎቹ ትዊቶች ግን አስቀያሚና የሚያሳዝኑ ነበሩ። ጥቂቶቹ እኔን እና ሌሎችን የሚያስፈራሩ ነበሩ። ጥቂቶቹ ቤተሰቤን ጠቀሱ። ከቁጥጥር ውጭ የሆነ ዘረኛ ዘለፋና ስድ ቃላት አጠቃቀም ነበር።

ይህ በማህበራዊ ሚድያ የተካሄደ ትግባሬ የሶስት ልጆች አባትና የ151,000 ልጆች የበላይ ተቆጣጣሪ እንደመሆኔ በሀላፊነቴ እና ልጆቻችን ቴክኖሎጂን በአግባቡ እንዲጠቀሙበት ለማረጋገጥ ሚናችን ምን እንደሆነ እንዳስብበት መነሻ ሆነ። የስልክ አልባ መገልገያዎች በተሟላ መዳረስና መገልገያህን-ይዘህ-ና ችሎታ ለልጆቻችን መፈቅድን ጨምሮ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም በት/ቤቶቻችን እየጨመርን በምንሄድበት ሁኔታ ይህን ጉዳይ በተለይ አስፈላጊ ያደርገዋል።

እንደ የበላይ ተቆጣጣሪነቴ፣ የ*in loco parentis (ወላጅን በመተካት)* ህጋዊ ሀላፊነት አለብኝ፣ ይህም ማለት በት/ቤት ህንፃ ውስጥ እኔና ሌሎች መምህራን እንደ "ወላጆች" ሆነን እንድናገለግል ይጠበቅብናል። አንዳንዶቹ ትዊቶች በጣም አሳሳቢ ከመሆናቸው የተነሳ ሰራተኞች ለት/ቤቱ ርእሰ መምህርና የፀጥታ ቡድናችን አመልክተዋቸዋል። ይህ ለተወሰኑ ሰዎች ከመጠን በላይ የተወሰደ አፀፋ ሊመስል ይችላል፣ ይሁን እንጂ እንደዚህ ማድረጉ ህጋዊ ሀላፊነታችን ነው፣ ጉዳዩን በአሳሳቢነት እንወስደዋለን።

ይህ ግን በፅ/ቤት ከፈተና በላይ ነው። ባለቤቴና እኔ በየቀኑ ከልጆቻችን ጋር ስለ  አግባብ ያለው ቴክኖሎጂ አጠቃቀም እንወያያለን መሳርያውን ለስንት ሰአት ይጠቀሙበታል? በቀን ስንት ጊዜ? የምን ፎቶግራፍ ማንሳት የቱ ይፈቀድላቸዋል፣ የቱስ አይፈቅድላቸውም? በይነመረብ ገና መዳረስ አይችሉም፣ ሲችሉ ግን ምን መሆን እንደሚችል ካሁኑ እየገመትኩ ነው። የመስመር ላይ አለምና ማህበራዊ ሚድያ በርካታ አወንታዊ ገፅታዎች ለመድረስ ሲፈቀድላቸው፣ ባለቤቴ እና እኔ እንዴት አድርገን ይሆን በመስመር ላይ ደህንነታቸው የምናረጋግጠው? በአግባቡ መገልገላቸውን ለማረጋገጥ ትክክለኛ ቁጥጥርና ግድፈት እንዳለን እንዴት አድርገን ነው የምናረጋግጠው?

በቤቴም ሆነ በት/ቤቶቻችን ለሁሉም መልሶች የሉኝም። ልጆች በቴክኖሎጂና በማህበራዊ ሚድያ እንዴት እንደሚጠቀሙ እንዲገነዘቡ ለማገዝ በአላማ የፀናና ጠንካራ ውይይቶች በቤተሰቦችና በማህበረሰብ ውስጥ ማካሄድ እንድሚያስፈልግ ግን እርግጠኛ ነኝ።

ተገቢ ያልሆኑ ትችቶች በትዊተር ለኔ የላኩ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች ያን ያደረጉት ሳያስቡ መሆኑን እርግጠኛ ነኝ። በውነቱ፣ የጎረምሳ አንጎል አርቆ ለማሰብ የታጠቀ አይደለም እናም  አዋቂዎች እንደሚያደርጉት የአደጋ/የሽልማት ሚዛን ስሌት እንደማያደርግ እናውቃለን። የተግባራቸውን ሰበብ ውጤት የሚገነዘቡ ቢሆኑ ኖሮ ወይም እኔ ዛቻዎችን ለፖሊስና ለወላጆቻቸው የማስታወቅ ህጋዊ ሃላፊነት እንዳለብኝ ቢያውቁ ኖሮ እነኚህን አይነቶች መልእክት ባላስተላለፉም ነበር ብዬ ማሰብ እፈልጋለሁ። በተለይም እነዚህ መልእክቶች ቋሚ እንደሆኑና ተከትለዋቸው በኮሌጅ መግቢያ፣ በስራ እድሎች፣ እና በወደፊት ግንኙነቶች ተፅእኖ እንደሚያደርጉ ቢገነዘቡ ኖሮ እነዚህን መልእክቶች ባላደረጉ ብዬ ማሰብ እፈልጋለሁ።

ይህን ደብዳቤ የፃፍኩት ልጆቻቻን ቴክኖሎጂን ጤናማ፣ ፍሬያማ፣ እና አወንታዊ በሆነ መንገድ እንዲጠቀሙበት እንዴት አድርገን ልንደግፋቸው እንደምንችል ውይይት ለመጀመር ነው። የኮምፒውተር-ዛቻ/ማስፈራርያ (Cyberbullying) በልጆችና በአዋቂዎች የእውነት አሳሳቢ ጉዳይ ነው። አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች እንዴት በአግባቡ እንደሚይዙ ልጆቻችንን ማስተማር ብቻ ሳይሆን፣ የገዛ ራሳችንን ስነምግባር በማህበራዊ ሚድያና በኢሜይል ሞዴል ማድረግ አለብን። ስለ "cybercivility" (የኮምፒውተር መልካም ስነምግባር) መነጋገር አለብን ልጆቻችን እንዴት አድርገው ሀላፊነት ወደሚሰማቸውና ተንከባካቢ አዋቂዎች እንደሚያድጉ እርስ በራሳቸውም በስነስርአትና በመከባበር እንዲገናኙ። ቤተሰቦች እነዚህን ውይይቶች እንደሚመሩ ለማገዝ ሰራተኞቼን የተወሰኑ ቁሳቁሶችና ዘይቤዎች እንዲያዘጋጁ ጠይቁአቸዋለሁ፣ ስለዚህ በዚህ ጉዳይ ተጨማሪ መረጃ በቅርቡ እንድምታገኙ ተጠባበቁ።

እስከዚያው ድረስ፣ በመስመር ላይ ምን ተገቢ እንደሆነና ምንስ ተገቢ እንዳልሆነ ልጆቻችሁን በተከታታይ እንድታነጋግሩ አሳስባችኋለሁ። በተጨማሪ፣ አስታውሱ፣ ልጃችሁ ከ13 በታች ከሆነ/ች፣ ማህበራዊ ሚድያ እንዲጠቀሙ አትፍቀዱላቸው—ለዚህ ዝግጁ አይደሉም ለአብዛኛዎቹ የታወቁ የማህበራዊ ሚድያ ጣብያዎች አጠቃቀም ስምምነቶች ወይም መመርያዎች ደንብ መጣስም ነው። ልጅዎ 13 ወይም ከዚህ በላይ ከሆነ/ች፣ እባካችሁን ማህበራዊ ሚድያን ለመጠቀም ዝግጁ እንደሆኑ አስቡበት። ገደቦች አስቀምጡ እናም ስለ የማህበራዊ ሚድያና ተንቀሳቃሽ (ሞባይል) ቴክኖሎጂ ተገቢ አጠቃቀም አነጋግሯቸው። እናም በመስመር ላይ ምን እንደሚለጥፉ/እንደሚልኩ መቆጣጠራችሁን አረጋግጡ።

የኛ ድር ጣብያ—www.montgomeryschoolsmd.org—ከልጆቻችሁ ጋር ለመነጋገር ልትጠቀሙባቸው የምትችሉ የተወሰኑ መጋልገያዎች አሉት እኛም በቅርብ ግዜ ተጨማሪ መገልገያዎች እናክልባቸዋለን። ይህን የcybercivility ንግግር ለማራመድ የሚያግዙ ሀሳቦች ወይም አስተያየቶች ካሏችሁ፣ እባካችሁ ለኔ በJoshua_Starr@mcpsmd.org ኢሜይል ለማድረግ ወይም በ@mcpssuper ትዊተር ላይ ለመገናኘት አትጠራጠሩ።

ከአክብሮት ጋር

Joshua P. Starr, Ed.D.
Superintendent of Schools

JPS:sln